

## ልዕልት ዙሪያሽ ገብረ እግዚአብሔር

**ጥቅምት 23 ቀን 1923 - መስከረም 8 ቀን 2013 ዓመተ ምሕረት**

ደሴ ድሬዳዋ አዲስአባ አሥመራ
ለሽር ሽር ይሁን ለመንግሥት ሥራ፣
በድፍን ኢትዮጵያ በየትም ይኹን የት
ባውሮፓ አሜሪካ ባራቱም ማዕዘናት
በምድሪቱ ዙሪያ እንዳልታየችበት
በልፍኝ ባዳራሹ እንዳልሞላችበት
በግቢ በፊትበር እንዳልወጣችበት፣



ካዲላክ ማርቸዲስ አማርጣ በያይነት
እንዳልኖረች ሁሉ በምቾት በድሎት
ጎዶሎ ቀን መጥቶ ኑሮዋን አጉድሎት
ለባዳ አገር ኑሮ ለስደት አብቅቷት፣
ጳጳሳት ካህናት መሣፍንት ወይዛዝርት
አገር ካገር ሰምቶ እጅቦ ስይሸኛት
በጓሮ በር ወጣች፣ ማንም ሰው ሳያያት።

ሰውነቱን እንጂ የት መጣን አትጠይቅ
ከትንሹ ትንሽ፣ ከትልቁ ትልቅ፣
ተናግራ አታስቀይም አጫውታ አትጠገብ
ፍቅርና ደስታካንደበቷ እሚዘንብ
የቀልድ የቁም ነገር የዕውቀት ማኅደር
የቁንጅ መለኪያ ውብና ሽቅርቅር
የማዕርግ ስሟ ምግብሯን የሚገልጥ
ልዕልት ዙሪያሽ ወርቅ የሰው ልክ የሰው ጌጥ
ኖሮ ኖሮ መሞት፣ የማይቀር ኾነና
ላትነቃ አንቀላፋች፣ ተኛች ተሸፋፍና።

እንኳንስ ልጆችሽ ዐይተን የማንጠግብሽ
እንኳን ዘመዶችሽ ከልብ የሚወዱሽ
እንኳን ወዳጆችሽ አለችን የሚሉሽ

አገልጋይ ጎረቤት ቀን ሲጎድልባቸው
ግራ እጅሽ ሳያየው፣ ቀኙ እየሰጣቸው
በከፉ በደጉ የደረስሽላቸው
ያገር ምድሩ እንባ አንደጎገርፍ ቢፈስ
ጨክና ኼዳለች ዙሪያሽ ላትመለስ።



**ቁጣውን ፈርቼ እንደሰው ባልወቅሰው**
**እግዜርን ታዘብኩት አሳዘነኝ ሥራው።**
**ከወሎ አፈር ዘግኖ በውሃዋ አቡክቶ**
**አጀብ ጉድ ያሰኘች ውብ እመቤት ሠርቶ፣**
**ከልካይ ባይኖርበት አታድርግ የሚለው**
**ያን የሚያምር ገላ ጨክኖ አፈረሰው።**

ምንም ብንመኘው ድምፅሽን
አንሰማም
ምንም ብንናፍቅ ዐይንሽን ዐናይም
ለገና ፋሲካ ልናይሽ አንመጣም
ገበታሽን ከበን ግብር አንበላም
ቤትሽ ባዶ ኾኗል ከንግዲህ የለሽም።

ዓይተን የማናውቀው ልዩ አመል አውጥተሽ
በርሽን ቆልፈሽ ጨክነሽ ከኼድሽ
ጉዞሽ ቀና ይሁን እንቅፋት አይምታሽ
ደህና ሁኚ እማማ አፈሩ ይቅለልሽ።

በጣም የናፈቁት የኼዱት ቀድመሽ
ባለቤትሽ ልጅሽ፣ አባትና አናትሽ
አያት ቅድመ አያቶች ወዳጅ ዘመዶችሽ
ልከንላቸዋል በክብር ይቀበሉሽ።

እስክንሰባሰብ ሁላችንም መጥተን
ክፉን ለክፋቱ ለክፉ ቀን ትተን
ሳቅና ጨዋታ ፍቅርሽን እያሰብን፣
በአጸደ ገነት እንዲያሳርፍልን
አምላክን በጸሎት እየተማጸንን
ትውልድ እንዳይረሳው በአክብሮት ይዘን
የሕወትሽን ገድል እንዘክረዋለን።

ደህና ሁኚ እማማ!!

ከልጆችሽ፣ ከልጅ ልጆችሽና፣ እንደእናትና አንደእህት ከሚወዱሽና ከሚያከብሩሽ፣
መለየትሽ መሪር ሀዘን ከሆነባቸው ዘመድ ወዳጆችሽ